# <u>ዕንባሽ ተናገረ!</u>

አሥራደው (ከፈረንሳይ)



ዘለላ ዘለላ ዱብ ዱብ በሚለው፤
ጉንጭሽን ሸርሽሮ ቁልቁል በሚፈሰው፤
ሳግ እንቅ አድርጎ በሚተናነቅሽ፤
በ'ንባሽ እያጠቀሰኩ ሰንኝ ቋጠርኩልሽ፤
ቃል ኪዳን ነውና አንብቢው አደራሽ::

ዕንባሽ ተናገረ !
ሆሄያት ቆጠረ፤
ውስጥሽን ፈልፍሎ እየመረመረ፤
ቃላትን አምጦ ሰንኞች ቋጠረ፤
ምሥጢሩን አወራ - መደበቁ ቀረ ::

አይምሮሽን ነድሎ - ልብሽን ሰርስሮ፤
ቆፍሮ ዐይኖችሽን - ጉንጭሽን ሸርሽሮ፤
አንጀትሽን ሞሽልቆ - ጨጓራሽን ልጦ፤
ቁልቁል በሚወርደው ደረትሽን አቋርጦ፤
ሳግ እንቅ አድርጎ በሚተናነቅሽ፤
በሚፈልቀው ኩሬ - እያጠቀሰኩ በንባሽ፤
ጥቂት ቃል ጻፍኩልሽ፤
አንብቢው አደራሽ ::

ዕንባሽ ተናገረ !
ፈደላት ቆጠረ፤
ውስጥሽን ፈልፍሎ እየመረመረ
ቃላትን አምጦ ሰንኞች ቋጠረ፤
ምሥጢሩን አወራ - ጩሆ ተናገረ ::

*ሃዘንሽ ፈንክቷት ብዕሬ ቆሰለች፤*
*ከግራ ወደቀኝ እየተወራጨች፤*
*ድምጿን ከፍ አድርጋ - እሪ ብላ ጮኸች፤*
*ባንቺ ዕንባ ተጠምቃ - ማተቧን ቋጠረች፤*
*ፊትሽን ለማበስ - ሮጠች ተሯሯጠች፤*
*ሃቅሽን አውጥታ - ጻፈች ቸከቸከች።*

*ያይኖችሽን ኩሬ ነድሎ በሚፈልቀው፤*
*ጅረት እንደ ዓባይ አቀብ በሚፈሰው፤*
*በሚገነፍለው እያጠቀሰኩ በ'ንባሽ፤*
*ይችን ጥቂት ሰንኝ ላንቺ ቋጠርኩልሽ፤*
*በ'ንባ የጨቀየ የራሰ ነው ብለሽ፤*
*እንዳትጠየፊ አንብቢው አደራሽ ።*

*ዕንባሽ ተናገረ !*
*ፈደላት ቆጠረ፤*
*ውሰጥሽን ፈልፍሎ እየመረመረ*
*ቃላትን አምጠ ሰንኞች ቋጠረ፤*
*ምሥጢሩን አወራ - ትንቢት ተናገረ ።*

*እናም :*
*ጻፍኩልሽ ! ጻፍኩልሽ ! እህቴ ልንገርሽ፤*
*እያጠቀሰኩ በ'ንባሽ፤*
*ተመኝቼ ሳቅሽን ዳግም እንዳታለቅሽ፤*
***እህቴ!***

*በሳውዲ አረቢያና፤ በመላ አረብ አገራት፤ ለሚሰቃዩ ኢትዮጵያዊ ወገኖቼ፤ ማስታወሻ ትሆን ዘንድ የተቋጨች ።*

*ጥቅምት 21/2006 ዓ.ም (October 31/2013)*